# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1994 በጀት ዓመት
## የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም
## ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1994

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1994 በጀት ዓመት
## የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም
## ሪፖርት

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1994

# ማ ው ጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ........................................................................ | 1 |
| 2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ ........................................................................ | 2 |
| 2.1 የሥነ-ሕዝብና ጤና (DHS) በተመለከተ ........................................ | 2 |
| 2.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የምርምር ውጤቶች ማስታወቂያ ሴሚናር...... | 3 |
| 2.3 የ1997 ዓ.ም አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅትን በተመለከተ................ | 3 |
| 2.4 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ................................................ | 4 |
| 2.5 የልጆች የስራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ........................................ | 4 |
| 2.6 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት....................................................... | 5 |
| 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ........................................................................ | 5 |
| 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት........................................ | 5 |
| 3.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ........................................ | 7 |
| 3.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት.................... | 9 |
| 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ ............................................ | 11 |
| 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ ............................................ | 11 |
| 4.2 የካርቶግራፊና የመዛግብት አያያዝ በተመለከተ ........................................ | 11 |
| 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ........................................ | 12 |
| 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና........................................................................ | 12 |
| 6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ........................................................ | 12 |
| 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ................................................ | 14 |
| 7. የበጀት አጠቃቀም........................................................................ | 15 |
| ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም........................................................ | 15 |
| ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም........................................................ | 16 |
| 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት ........................................ | 18 |
| 8.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች ........................................ | 18 |
| 8.2 ትራንስፖርትና ጥገናን በተመለከተ................................................ | 18 |
| 8.3 ሕትመት ........................................................................ | 19 |
| 8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ ........................................ | 19 |
| 9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................................ | 22 |

# የ1994 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት
# የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የአገሮችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልማት ፖሊሲዎች እንዲሁም የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን ለማዘጋጀት የስታቲስቲካዊ መረጃዎች ጠቀሜታ እያደገ መጥቷል። በመሆኑም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ባለፉት አራት አስርት ዓመታት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ - ነክ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመገምገምና በመተንተን ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ያሰራጨ ሲሆን፣ አሁንም በማሰራጨት ላይ ይገኛል። እነዚህን መረጃዎች ለማዘጋጀት ከመንግሥትና ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በርካታ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሙያ ድጋፍ ለባለሥልጣኑ የተሰጠ ሲሆን፣ የጥናቶቹም ይዘትና የጥራት ደረጃ እያደገ እንዲሄድ ጥረት ተደርጓል።

በ1994 በጀት ዓመት በሁለት ፕሮጀክቶች ስር የሚካሄዱ በርካታ ጥናቶች በባለሥልጣኑ መ/ቤት ለማካሄድ በዕቅድ የተያዘና ሥራቸውም የተጀመረ ሲሆን፣ በተለይም ለአገራችን አዲስና በጣም በርካታ የሰው ኃይል፣ ቁሳቁስና በጀት የተያዘለት የኢትዮጵያ የግብርና ናሙና ቆጠራ ዋነኛው ነው። በዚህ ቆጠራ በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎችና በናሙና በተመረጡ ከ12 ሺህ በላይ የቆጠራ ቦታዎች የሚሸፈኑ ሲሆን፣ ከቆጠራው የሚገኘው ውጤትም አስተማማኝና ከዚህ በፊት ከወጡት የግብርና መረጃዎች የተሻለ ሽፋን እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል። በቆጠራው የገጠር፣ የከተማ፣ የሰፋፊና መካከለኛ የንግድና የመንግሥት እርሻዎች እንደዚሁም የአርብቶ አደሩ አካባቢዎችም እንዲሸፈኑ ይደረጋል።

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ የሚጠኑ ጥናቶችና ባለፈው ዓመት የተጀመሩ ጥናቶች የሪፖርት ሥራ ሙሉ በሙሉ የሚጠናቀቅ ሲሆን፣ ጥናቶቹም የሚከተሉትን ያጠቃልላል። እነዚህም:-

ሀ. የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- የግብርና የገጠር የግል ባለይዞታዎች ጥናት (የመኸርና የበልግ፣ የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ቆጠራ)፣
- የከተማ አካባቢ የግብርና ቆጠራ፣
- የሰፋፊና መካከለኛ የግል፣ የመንግሥትና የማህበራት እርሻዎች ቆጠራ፣ እና
- የአርብቶ አደር አካባቢ የግብርና ቆጠራ ናቸው።

ለ. የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የመካከለኛ፣ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት፣ እና
- የዋጋዎች ኢንዴክስ ዝግጅት ናቸው።

ሐ. በ1993 ዓ.ም የተጀመሩና በዕቅድ ዓመቱ የሚጠናቀቁ የጥናት ሪፖርቶች

- የመካከለኛ፣ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ እና
- የሕፃናት የሥራ ሁኔታ ( Stand - alone Child Labour) ጥናት፣ ናቸው።

በ1994 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች ለማከናወን በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተደረገውን የሥራ እንቅስቃሴ በዝርዝር በዚህ ሪፖርት ውስጥ ለማካተት የተሞከረ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራት ተጠቃለው ቀርበዋል። እንዲሁም በሩብ ዓመቱ በዕቅድ አፈፃፀሙ ያጋጠሙ ችግሮች፣ ለችግሮቹ በባለሥልጣኑ የተሰጡ መፍትሄዎችና በበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 2. <u>የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በተለያዩ ዘርፎች ያለውን የመረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ሲሆን፣ በተለያዩ ወቅቶች ሕዝብ ነክ ጥናቶችን በማካሄድ ተከታታይ የመረጃ ሪፖርቶችን ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል። በመሆኑም በ1994 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል።

### 2.1 <u>የሥነ - ሕዝብና ጤና ጥናትን (DHS) በተመለከተ</u>

<u>የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ዋናውን ሪፖርት ለክልሎች ማስተዋወቂያ ሴሚናር ዝግጅት</u>

የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ዋናው ሪፖርት በአገር አቀፍ ደረጃ የአንድ ቀን የማስተዋወቂያ ሴሚናር ቀደም ብሎ መካሄዱ ይታወቃል። በተመሣሣይ ሁኔታ ይህንኑ ሪፖርት በተመለከተ ለሁሉም ክልሎች የማስተዋወቂያ ዓውደ ጥናቶችን ማካሄድ በማስፈለጉ አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ በክልል ደረጃ የተዘጋጁ ሪፖርቶችን ሕትመት፣ ለሴሚናሩ የ"Power Point" ዝግጅቶች፣

የሴሚናሩን ስፍራ መምረጥና የተሳታፊዎችን ዝርዝር ማዘጋጀት የመሳሰሉት ተጠናቀዋል። እንዲሁም ለሴሚናሩ በመጀመሪያው ዙር አዲስ አበባ፣ ኦሮሚያ፣ አማራና የደቡብ ክልሎች የተመረጡ ሲሆን፣ ዝግጅቶቹም የሚካሄዱት ከክልሎቹ የሥነ ሕዝብ ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ይሆናል። የሴሚናሩ ቀንም በቅርቡ እንደሚወሰን ይጠበቃል።

## 2.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የምርምር ውጤቶች ማስተዋወቂያ ሴሚናር፣

መ/ቤቱ ከጣሊያን አገር ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሚገኘው የሥነ ሕዝብ ማሠልጠኛ ማዕከል ጋር በመተባበር ሰባት የምርምር ጽሑፎችን ያዘጋጀ ሲሆን፣ ጽሑፎቹን ለሕዝብ ለማስተዋወቅም የአንድ ቀን ሴሚናር በአዲስ አበባ የተባበሩት መንግሥታት የስብሰባ ማዕከል አካሂዷል። በስብሰባው ከጣሊያን አገር የመጡ ምሁራንና የመ/ቤቱ ባልደረቦች ጽሑፎችን በማቅረብ ተሳትፈዋል። በአሁኑ ጊዜ የምርምር ውጤቶቹን ጽሑፎች የማዘጋጀቱ ተግባር እየተጠናቀቀ ሲሆን በቅርቡ ለሕትመት ይላካል።

## 2.3 የ1997 አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅት

- በ1997 ለሚካሄደው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል። አብዛኛው ሥራ በቅድመ ቆጠራ የካርታ ሥራ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በዚህ መጠነ ሰፊ የካርታ ሥራ ወቅት የሚገኘውን መረጃ በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል የካርታ ሥራውን ኮምፒዩተራይዝ ለማድረግ ኮምፒውተሮች፣ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች፣ ዲጂታይዘሮች፣ ስካነሮች፣ ፕሎተሮችና ትላልቅ ከለር ፕሪንተሮች ከውጪ አገር በUNFPA ዕርዳታ ታዝው አብዛኛዎቹን ርክክብ ተፈፅሟል። በተጨማሪም ለካርታ ሥራው መገዛት ያለባቸው GPS, Plan Printer, Digital area Calculator, Lettering System, Drawing Sets, Drawing Pens, Tracing Paper, ፎቶ ኮፒየሮችና ዲጂታል ኤርያ ካልኩሌተር ከውጪ አገር በUNFPA በኩል እንዲገዙ ተደርጎ ከፊሎቹን ተረክበናል።

- ለካርታ ሥራው የመስክ ሥራና ለዋናው ቆጠራ ጭምር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዝርዝርና አጠቃላይ የፕሮጀክት ዶክመንት ዝግጅት ከUNFPA CST ከተመደ ባለሙያ ጋር በመተባበር ተዘጋጅቷል። ይህ ፕሮጀክት ዶክመንት

ለመንግሥትና ለለጋሽ ድርጅቶች ሁሉ እንዲደርስ የሚደረግ ሲሆን፣ ለመንግሥት በሚቀርበው የበጀት ፍላጎትና አጠቃቀም ላይ የሥራውን መርሃ ግብር እንዲያሣይ ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

- የUNFPA አራተኛው ዙር የዕርዳታ ፕሮግራም በ Dec.2001 ስለሚጠናቀቅ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የሚያገለግል የዕርዳታ ፕሮግራም በመዘጋጀት ላይ ሲሆን፣ በቀጣዩ ዙር ፕሮግራም ዝግጅት መ/ቤቱ በአባልነት ተወክሎ በመሣተፍ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት መ/ቤቱ ለቀጣዩ የ1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራ አስፈላጊው ዕርዳታ እንዲገኝ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

## 2.4 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ

- የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲካል የሙከራ የጥናት ቦታዎችን ለመፍጠርም ሆነ ከአስፈፃሚ ተቋማቱ ጋር ለመሥራት የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶችን የሚገልጽ "በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የተዘጋጀ ዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ" ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የዚሁ ስታቲስቲክስ የመዝጋቢዎች መመሪያ ሶስተኛ ረቂቅ ለአስተያየት የቀረበ ሲሆን፣ መመሪያው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅጾችን ይዘቱ፣ የምስክር ወረቀቶችንና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን የያዘ ነው።

- ከምዝገባውና ከወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ቅጾች ላይ ሊጠናቀሩ የሚችሉ የመረጃ ሠንጠረዦች ዝርዝሮች (Proposed List of Tables) በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅተዋል።

## 2.5 የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ

በ1993 ዓ.ም ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ከዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር የልጆች የሥራ ሁኔታ ጥናት (Stand Alone Child Labour Survey) እንዲያካሂድ በጠየቁት መሠረት የጥናቱ የመስክ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ መከናወኑ ይታወቃል። ይህን ጥናት አስመልክቶ ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ፡-

- የመረጃ ኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ሥራ ተጠናቋል፣

- መረጃ የማጽዳት (Cleaning) እና መረጃውን በኮምፒውተር ለማጠናቀር የፕሮግራም ዝግጅትና የፕሮሰሲንግ ሥራ ተከናውኗል፣

- ለጥናቱ በተዘጋጀው ዌይት (weight) በመጠቀም የሕዝብ ብዛት የሚያሳዩ ሠንጠረዦች የወጡ ሲሆን፣ ይህንኑ መረጃ ከሌሎች የጥናት ውጤቶች ጋር ለማነፃፀር ተሞክሯል፣ እና

- የጥናቱንም ውጤት ለመተንተን የተለያዩ ሀገሮችን ልምድ ለማግኘት ከአዲስ አበባ የILO መ/ቤት ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ በተጨማሪም የባለሙያ ድጋፍ በድርጅቱ በኩል የሚገኝበት መንገድ እየተሞከረ ይገኛል።

## 2.6 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ከተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ግለሰብ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡበትን ጥያቄዎች በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ቴክኒካዊ ድጋፍ አድርጓል።

# 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጫቸው የጥናት ሪፖርቶች አብዛኛዎቹ የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ዘርፍ ጥናት ውጤቶች ናቸው። በዚህ በጀት ዓመትም በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምና በግብርና ናሙና ቆጠራ አማካይነት ከሚከናወኑት የተለያዩ ጥናቶች ዘርፉን የሚመለከቱ የጥናት ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ በ1994 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በዘርፉ የተከናወኑ ሥራዎችን የዕቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል።

## 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.1.1 ዓመታዊ የግብርና ናሙና ጥናት

ሀ. የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

በ1994 ዓ.ም ከመስከረም ጀምሮ ለተካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ ቅንብር የሚያገለግል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል።

ለ. <u>የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ</u>

1993 የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

ሐ. <u>የእርሻ ሥራን /Farm Management Practices/ በተመለከተ</u>

የ1993 ዓ.ም የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ በሕትመት ላይ ይገኛል::

መ. <u>መሬት አጠቃቀምን / Land Utilization/ በተመለከተ</u>

የ1993 የመሬት አጠቃቀም ሪፖርት የሚሆነው መረጃ ከመስክ ተሰብስቦና ተቀነባብሮ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት የተዘጋጀ ሲሆን፣ የመረጃው አስተማማኝነት ግምገማው በግብርና ቆጠራው ሥራ ምክንያት ሊጠናቀቅ አልቻለም::

ሠ. <u>የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

በ1993 ዓ.ም በየካቲት ወር በተካሄደው የቤት እንስሳት ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራው ተጠናቆ የመረጃ ቅንብሩም ሥራ ተጠናቋል:: ሆኖም የመረጃው አስተማማኝነት ግምገማው በግብርና ቆጠራ ሥራ ምክንያት ሊጠናቀቅ አልቻለም::

3.1.2 <u>የ1994 የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራን በተመለከተ</u>

ይህ የቆጠራ ተግባር በመላ አገሪቱ በ 465 ወረዳዎች ውስጥ በገጠር በናሙና በተመረጡ 11,257 የቆጠራ ቦታዎች፣ ወደ 16,000 የሚጠጋ የሰው ኃይል በማሰማራት ከመስከረም 2 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በመስክ መረጃ የመሰብሰቡ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

ሀ. የግብርና ናሙና ቆጠራ ለሚሳተፉ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና የሚውሉና በመስክ ለመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የሚውሉ የቆጠራ ዶክመንቶች ማለትም መጠይቆ፣ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ቅጾች እንዲሁም የመስክ መገልገያ

መሳሪያዎች ሥርጭት የሚውል ዝርዝር በማዘጋጀት ለግብርና ናሙና ቆጠራ የትራንስፖርት ኮሚቴና ሎጂስቲክስ ኮሚቴ አስተላልፏል።

ለ. ለ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ ግብርና ቆጠራ መረጃ ቅንብር የሚያገለግል የአካባቢ የስፋትና የምርት መጠን መለኪያዎች (Local Area and Production Units) ኮድ ቡክ ዝግጅት ተጠናቋል።

ሐ. በግብርና ናሙና ቆጠራ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ወቅትና በሰብል ትንበያ መረጃ መሰብሰብ ወቅት ከሁሉም የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለቆጠራው አፈፃፀም ተነስተው ለነበሩ በርካታ የቴክኒክና ተዛማጅ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።

መ. ለነባር ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ስለግብርና ናሙና ቆጠራው አጠቃላይ ይዘትና የቴክኒክ አሠራሩን በተመለከተ የአራት ቀናት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት እንዲሰጣቸው ተደርጓል።

### 3.1.3 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

- በ1994 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ኮሚቴዎች በአባልነት፣ በቆጠራው ለሚሰማሩ መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች በአሠልጣኝነት እንዲሁም በመስከረም ወር በተካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ላይ በመስክ ሥራ ቁጥጥርና ግምገማ ተሳታፊ ሆነዋል።

- ከተለያዩ ድርጅቶች የሚመጡ የመረጃ ተጠቃሚዎች ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና የስታቲስቲካዊ መረጃ አጠቃቀም ላይ ተገቢውን የሙያ ድጋፍ አድርገዋል።

## 3.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶችን ሥራ በተመለከተ

ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት

- ከሚያዚያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ድረስ ያሉት መረጃዎች የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ነው።

- ከሐምሌ 1993 እስከ ነሐሴ 1993 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ ስብሰባ ተግባር በኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ ሥልጠና ምክንያት ያልተከናወነ ሲሆን፣ የመስከረም ወር 1994 ዓ.ም መረጃ ከመስከ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል።

ለ. <u>በገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- የሚያዚያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ያለው መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ነው።

- የገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ ሲሰበሰብ የነበረው የገበያ ቦታዎችን ስርጭት በተከተለ መልኩ ሳይሆን ለግብርና ናሙና ጥናት በሚመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ነዋሪ የሆኑ ቤተሰቦች የሚገበያዩባቸው ገበያዎች ላይ ያተኮረ እንደነበረ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የገጠሩ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ስርዓት አንፃር ሲገመገም ጠቀሜታው የጎላ አልሆነም። በተለይም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንደክስን ለማስላት የተመረጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (Basket of Commodities) በእነዚህ የገጠር ገበያዎች በአብዛኛው አለመገኘት ሳቢያ የገጠር ችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሐምሌ 1993 ጀምሮ እንዲቋረጥ ተደርጓል። በመሆኑም ከየዞኑ የደራ ገበያ ቦታዎችን በመምረጥ የጥናቱን አድማስ በማስፋት ረገድ ከዚህ ቀደም በ45 ከተሞች ብቻ ይካሄድ የነበረውን የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ወደ 106 ከተሞች ከፍ እንዲል በማድረግ ከእነዚህ ከተሞች ከሚሰበሰበው መረጃ አማካይነት በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ለእያንዳንዱ ክልል የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ለመሥራት ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ነው።

ሐ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- <u>በ45 ከተሞች የሚካሄደው ነባር የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

ከሐምሌ 1992 እስከ - መጋቢት 1993 ዓ.ም. ድረስ ያለው መረጃ ሪፖርት ተጠናቅቆ ለሕትመት የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከሚያዝያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ድረስ ያለው መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቅቆ የመረጃ ቅንብር ሥራ በመከናወን ላይ ነው።

- <u>በ106 ከተሞች የሚካሄደው አዲስ የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

  - በ106 ከተሞች ውስጥ በሚገኙ 119 የገበያ ቦታዎች የሚካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት የሐምሌ ወር መረጃ የዳታ ፕሮሴሲንግ ሥራ ተጠናቋል::

  - የነሐሴ ወር 1993 ዓ.ም የዳታ ክሊኒንግ ሥራ እየተካሄደ ሲሆን የመስከረም ወር 1994 ደግሞ የመረጃ መሰባሰቡ ተግባር ተጠናቋል::

መ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ</u>

- <u>ነባር የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ</u>

ከዚህ ቀደም ሲሠሩ የነበሩ የአገር አቀፍ፣ የገጠርና የከተማ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶችን በተመለከተ እስከ ሰኔ ወር 1993 ዓ.ም. ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፣ ከሐምሌ ወር 1993 ዓ.ም ጀምሮ የገበያዎች ለውጥ በመደረጉ ከላይ የተጠቀሱት ኢንዴክሶች አልተዘጋጁም::

- <u>የአዲስ አበባ ከተማ ኢንዴክስ</u>

አዲሱን የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት እንዲቻል በቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ወቅት የተገኘውን የወጪ መጠን የመቶኛ ድርሻ (weight) በመውሰድ ታህሣሥ ወር 1993ን ዓ.ም መሠረት አድርጎ ለመሥራት ከለሳ በመካሄድ ላይ ነው:: በመሆኑም አዲሱን ኢንዴክስ ለእያንዳንዱ ክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ለመሥራት እንዲቻል የweight ከለሳው ለ6 ክልሎች የተከናወነ ሲሆን፣ የዕቃዎችና አገልግሎቶች (Basket of commoditiies) መረጣ ተጠናቋል::

## 3.3 <u>የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

### 3.3.1 <u>የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

የ1992 ዓ.ም የዘርፉ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ፣ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ የሠንጠረዥ ቅንብር ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለሕትመት በሚሆን መልኩ በመዘጋጀት ላይ ነው::

ለ. <u>የኢሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃን በሚመለከት፡</u>

የ1992 መረጃም ከመስከ ተሰብስቦ በዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻና የኢሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መጽሔት ውስጥ ተካትቶ እንዲወጣ ለማድረግ መረጃው በመጠናቀር ላይ ይገኛል።

ሐ. <u>የውጭ የንግድ፣ የትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃ፡</u>

- አ.አ.አ የ2000ን መረጃ የያዘው የወጪ ንግድ መጽሔት በሕትመት ላይ ይገኛል።

- አ.አ.አ የ2001 የውጭ ንግድ መረጃ እስከ June 2001 ያለው ተሰብስቦ የመረጃ ቅንብር ሥራው ተጠናቋል።

መ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

- <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ኢንዴክስ ሥራ</u>

  – የ1992ን ዓ.ም መረጃ የሚያካትተው የኢንዴክስ ሥራ የመረጃ ቅንብር ሥራ በመሠራት ላይ ነው።

  – በተጨማሪም በሁሉም ዘርፎች እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጎት ለማሟላት ለተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠትና አጠቃቀሙን የማስረዳት ሥራ ተከናውኗል።

## በ1994 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የጥናቶች የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

ሠንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1993 በጀት ዓመት መጨረሻ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ | | | | | |
| 1.1 | የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት | አዲስ | 15 | 45 | 45 | 100 |
| 1.2 | የዋናው መኸር ወቅት የግብርና ቆጠራ ጥናት | አዲስ | 15 | 7.08 | 7.08 | 100 |
| 2. | የዋጋዎች ጥናት | | | | | |
| 2.1 | የ1993 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | ነባር | 95 | 5 | 5 | 100 |
| 2.2 | የ1994 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ በገጠር | አዲስ | 15 | 20.6 | 20.6 | 100 |
| 2.3 | የ1994 የአምራቾች የችርቻሮ ዋጋ ከተማ | አዲስ | 15 | 20.6 | 20.6 | 100 |
| 3 | የ1992 የትላል. የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | ነባር | 87.6 | 12.4 | 11.2 | 90 |
| 4 | የ1993 የትላል. የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | አዲስ | - | 2.8 | 2.8 | 100 |
| 5 | የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት | አዲስ | 10.7 | 4.3 | 3.1 | 72 |
| 6. | ዋጋዎች ኢንዴክስ ሥራ | | | | | |
| 6.1 | የአዲስ አበባ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 25 | 25 | 100 |
| 6.2 | የአገር አቀፍ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 22.5 | 22.5 | 100 |

## 4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ

- የ1993 ዓ.ም የልጆች ሥራ ስምሪት ናሙና ጥናት አስመልክቶ የማባዣ ሥራ ተሰርቶና ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል፡፡

- ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ዶክመንቶችንና ለCrop forecast የሚያስፈልገውን የ raising factor ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

### 4.1 ካርቶግራፊና መዛግብት አያያዝ

ለግብርና ቆጠራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ የቆጠራ ካርታዎችና የወረዳ ካርታዎችን ለይቶ በማውጣት አሳትሞ ለሚመለከተው ክፍል በመስጠት በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡

5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ-ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች ለሚይዘው ለዚህ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመሰብሰብ ተግባር ተጀምሯል። በመሆኑም ዓመታዊ መጽሔቱ በሚዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲያካትት የሚደረግ ሲሆን እነዚህም፡-

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሀገር ሀብት መረጃዎች፣
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የውጭ አገር ንግድ መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

# 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

## 6.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ

በ1994 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,480 ቋሚና 1,665 የኮንትራት በጠቅላላው 3,145 ሠራተኞች ነበሩ ። ከነዚህ ቋሚ የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ውስጥ ባለፉት ሦስት ወራት 19 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ ሥራቸውን የለቀቁ፣ 17 ሠራተኞች በሞት የተለዩ እንደዚሁም 2 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ ሲሆን የ 8 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል። በሌላ በኩል ከነበሩት የኮንትራት የሰው ኃይል ውስጥ 12,397 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 734 ሱፐርቫይዘሮች፣ 7 ጊዜያዊ የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎች፣ 142 የአስተዳደርና የሒሳብ ሠራተኞች እንደዚሁም 18 ሹፌሮች በድምሩ 13,289 አዲስ የኮንትራት ሠራተኞች ሲቀጠሩ 3 ሠራተኞች በሞትና 108 ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ተሰናብተዋል።

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 16,302 ሲሆን፣ ከእነዚህ መሐል 1,450 ቋሚና 14,852 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ሩብ ዓመት መጨረሻ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል፡፡

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

<u>ሠንጠረዥ 2</u>

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቁጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,480 | 1,665 | 3,145 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 8 | 13,298 | 13,306 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (2) | - | (2) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (19) | (108) | (127) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (17) | (3) | (20) |
| ድምር | | 1,450 | 14,852 | 16,302 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 125 ፕሮፌሽናል፣ 925 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 400 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው፡፡ የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,100 ወንዶች /75.9 በመቶ/ ሲሆን 350 ሴቶች /24.1 በመቶ/ ናቸው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የኮንትራት ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 66 ፕሮፌሽናል፣ 14,456 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 330 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ በፆታ ሲለዩ ደግሞ 11,837 ወንዶች /79.7 በመቶ/ 3,015 ሴቶች /20.3 በመቶ /ናቸው፡፡

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ</u>

<u>ሠንጠረዥ 3</u>

| ፆታ | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌ ሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | |
| ወንድ | 109 | 817 | 174 | 1,100 | 61 | 11,479 | 297 | 11,837 | 12,937 |
| ሴት | 16 | 108 | 226 | 350 | 5 | 2,977 | 33 | 3,015 | 3,365 |
| ድምር | 125 | 925 | 400 | 1,450 | 66 | 14,456 | 330 | 14,852 | 16,302 |

6.2 <u>የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየጊዜው ለሚያካሂዳቸው አዳዲስና ነባር ጥናቶች ያሉትን ባለሙያዎች ወቅታዊ የሆነ ሥልጠና በመስጠት ሙያቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል። በመሆኑም በ1994 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል።

ሀ. በዚህ ዓመት በአዲስ መልክ ለተጀመረው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከመላው ሀገሪቱ ከተመረጡ 120 የገበያ ቦታዎች መረጃ ለሚሰበስቡ ሠልጣኞች ከሰኔ 20 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት የተሰጣቸው ሲሆን፣ ሠልጣኞቹም ወደተመደቡበት የገበያ ቦታ ተሠማርተው ወርሃዊ መረጃ በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ።

ለ. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በአዲስ አበባ በሁለት ማሰልጠኛ ማዕከላት ከዋናው መ/ቤት፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከሌሎች መ/ቤቶች ለተውጣጡ 542 ባለሙያዎች ከሰኔ 5 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ የአሠልጣኞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ሁኔታ ከሐምሌ 13 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 23 ቀን 1993 ዓ.ም በ47 የተመረጡ የሥልጠና ማዕከላት ለ13,100 የመረጃ ሰብሳቢዎችን ለ2,430 ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና በመስጠት፣ ነሐሴ 24 ቀን 1993 ዓ.ም በማዕከል በተዘጋጀ የመመዘኛ ፈተና ውጤት መሠረት ብቃት ያላቸው ለመስክ ሥራው ተመርጠው በሥራ ላይ ይገኛሉ።

ሐ. በ1993 ዓ.ም ለአንድ ዓመት በጋና ሀገር የማስተርስ ዲግሪ ትምህርት የተከታተሉ ሁለት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ጨረሰው የተመለሱ ሲሆን፣ በተመሳሳይ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከነበሩት መካከል ሦስቱ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደሥራ ተሰማርተዋል። እንዲሁም ሌሎች ሦስት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ።

መ. በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የመ/ቤቱን ሠራተኞች የሥራ ብቃት ለመሻሻል በነበረው ዕቅድ መሠረት ሦስት ሠራተኞች በሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት ለ5 ቀናት የቢሮ አያያዝ ሥልጠና ወስደው እንዲመለሱ ተደርጓል።

7. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ለ1994 በጀት ዓመት ለአጠቃላይ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል ወጪ ብር 147,850,200 በዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 12,485,500 ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 135,364,700 ተፈቅዷል:: ከተፈቀደው በጀት ውስጥ 8.45% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን፣ 91.55% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው::

ሀ. <u>የመደበኛ በጀት አጠቃቀም</u>

የተፈቀደው በጀት በሚከተለው የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው:: ይኸውም:-

- ለደመወዝ .................ብር 11,130,700.00
- ለውሎ አበል ..............." 40,000.00
- ለሥራ ማስኬጃ ............." 1,314,800.00 የተያዘ ነው::

በሦስት ወራት ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው መጠን:-

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው 11,130,500 ብር ውስጥ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 2,276,268 ሲሆን፣ ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ መስከረም 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ከተፈቀደው ብር 2,276,268 (100%) ወጪ ተደርጓል::

- ለውሎ አበል ክፍያ ከተፈቀደው ብር 40,000.00 ውስጥ ባለፉት ሦስት ወራት ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 3,400 ሲሆን፣ ከተፈቀደው ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 2,285 (67.20%) ይሆናል::

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው 1,314,800 ብር ውስጥ ላለፉት ሦስት ወራት ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 63,400 ሲሆን፣ ከተፈቀደው ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 227,247.65 ነው::

ለ1994 በጀት ዓመት ሦስት ወራት ውስጥ ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ መስከረም 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለመደበኛ በጀት በእጅ ገቢ የሆነው ብር 2,343,068 ሲሆን፣ ወጪ የሆነው ብር 2,505,800 ነው:: አፈፃፀሙ በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀር 106.9% ሲሆን ከዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ደግሞ 20.0 % ይሆናል::

ለ. <u>የካፒታል በጀት አጠቃቀም</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1994 ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮግራሞች ብር 135,364,700.00 የተፈቀደ ሲሆን፣ ይህም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 3,383,900.00 ፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ፕሮግራም ደግሞ ብር 131,980,800 የተፈቀደ ነው።

ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ መስከረም 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 401,900.00 (11.87%) ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ደግሞ ከተፈቀደው ብር 38,202,659 (28.94) ወጪ ሆኖ በሥራ ላይ ውሏል። ለሁለቱ ፕሮግራሞች ከተፈቀደው በጀት በሦስት ወራት ውስጥ በጠቅላላ ወጪ የሆነው ብር 38,604,559 ( 28.5%) ነው።

የመደበኛና የካፒታል በጀት በሦስት ወራት ውስጥ ብር 45,120,248 ተጠይቆ በእጅ የገባ ሲሆን፣ ብር 41,110,359 ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ወጪ የተደረገው በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀርም 91.1 በመቶ ይሆናል። አሃዛዊ መረጃውም በሠንጠረዥ 4 ላይ ተመልክቷል።

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ1994 ዓ.ም የ1ኛ ሩብ ዓመት በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 4

| ተ.ቁ | የበጀት አጠቃቀም | የበጀት ኮድ | ለ1994 ዓ.ም ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | በሩብ ዓመቱ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት /በ04 እና 05 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 00 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 |
| 1 | ለመደበኛ በጀት | | 12,485,500 | 2,343,068 | 2,505,800 | (162,732) |
| 1.1 | ለሠራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች | 6110 | 11,130,500 | 2,276,268 | 2,276,268 | - |
| 1.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 451,200 | | 111,487 | (111,487) |
| 1.3 | ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርት... ወዘተ | 6230 | 58,300 | 4,800 | 8,503 | (3,703) |
| 1.4 | ለዕድሳትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 355,500 | 29,600 | 76,586 | (46,986) |
| 1.5 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎት | 6251 | 389,800 | 32,400 | 30,756 | 1,644 |
| 1.6 | ለቋሚ ንብረቶች | 6310 | 100,000 | | 2,200 | (2,200) |
| 2 | ለካፒታል በጀት | | 135,364,700 | 42,777,180 | 38,604,559 | 4,172,621 |
| 2.1 | ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ | | 3,383,900 | 587,908 | 401,900 | 186,008 |
| 2.1.1 | ለሠራተኞች የሚከፈሉ ክፍያዎች | 6110 | 907,900 | 184,808 | 196,000 | (11,192) |
| 2.1.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 753,000 | 106,600 | 51,200 | 55,400 |
| 2.1.3 | ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርት... ወዘተ | 6230 | 555,600 | 149,700 | 88,900 | 60,800 |
| 2.1.4 | ለዕድሳትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 579,200 | 40,000 | - | 40,000 |
| 2.1.5 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎት | 6251 | 488,200 | 106,800 | 65,800 | 41,000 |
| 2.1.6 | ለአገር ውስጥ ስልጠና | 6271 | 100,000 | - | - | - |
| 2.2 | ለግብርና ናሙና ቆጠራ | | 131,980,800 | 42,189,272 | 38,202,659 | 3,986,613 |
| 2.2.1 | ለሠራተኞች የሚፈሉ ክፍያዎች | 6110 | 65,093,300 | 10,848,884 | 9,659,638 | 1,189,246 |
| 2.2.2 | ለአላቂ ዕቃዎችና መሣሪያዎች | 6210 | 6,361,100 | 2,400,290 | 766,208 | 1,634,082 |
| 2.2.3 | ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርት... ወዘተ | 6230 | 47,537,500 | 24,776,185 | 26,258,511 | (1,482,326) |
| 2.2.4 | ለዕድሳትና ጥገና አገልግሎት | 6240 | 6,250,00 | 1,047,280 | 1,044,161 | 3,119 |
| 2.2.5 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎት | 6251 | 6,593,900 | 2,944,633 | 368,611 | 2,576,022 |
| 2.2.6 | በቋሚ ንብረት | 6310 | 145,000 | 145,000 | 105,530 | 39,470 |
| | ጠቅላላ ድምር | | 147,850,200 | 45,120,248 | 41,110,359 | 4,009,889 |

## 8. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

በባለሥልጣኑ መ/ቤት ያሉት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በዕቅድ ለተያዙት በሁለት ፕሮጀክቶች ስር ላሉ ጥናቶች እገዛ የሚያደርጉ ሥራዎችን አከናውነዋል:: ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 8.1 የዕቃ ግዥን በተመለከተ

ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ መስከረም 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት እንዲውሉ ብር 9,349,713.72 ወጪ ተደርጎ የተለያዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም የአገልግሎት ግዢዎች ተፈፅሟል:: ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል::

**በ1994 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተፈፀመ ግዢ**

ሠንጠረዥ 5

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት /የአገልግሎቱ ዓይነት | የገንዘብ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| 1 | የኮምፒውተር ዕቃዎች፣ ፕሪንተሮችና ተዛማጅ ዕቃዎች | 374,460 | 00 |
| 2 | የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች | 49,574 | 73 |
| 3 | የጽሕፈት መሣሪያ | 681,071 | 73 |
| 4 | ለግብርና ቆጠራ የተገዙ ዕቃዎች(በጥቅል) | 805,768 | 00 |
| 5 | ለግብርና ቆጠራ መጠይቅና ፖስተር የታተመበት | 424,366 | 75 |
| 6 | የተለያዩ የጥገና ዕቃዎች | 5,972 | 20 |
| 7 | በዕርዳታ ለተገኙ ዕቃዎች የቀረጥ፣ ለኪራይና ዲክላራሲዮን | 6,909,267 | 62 |
| 8 | ለማስታወቂያና ለጋዜጦች ግዢ | 12,682 | 20 |
| 9 | ልዩ ልዩ ወጪዎች | 3,843 | 20 |
| 10 | የቆጠራ ዶክመንት ለማጓጓዝ የተከፈለ | 82,709 | 00 |
| | ድምር | 9,349,713 | 72 |

### 8.2 ትራንስፖርትና ጥገና

- በመንግሥት በጀት ለኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተገዙ 42 የመስክ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራና ሠሌዳ በማስወጣት ለቆጠራው አገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፣

- 60 የመስከ ተሸከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎላቸው ለሥራ ተሰማርተዋል፣

- 45 የመስከ ተሸከርካሪዎች ከባድና መለስተኛ ጥገናዎች እንዲሁም ሰርቪስ በዋናው መ/ቤት ተደርጎላቸው ለሥራ ተሰማሩ ሲሆን፣ ለእነዚህም ተሸከርካሪዎች በሩብ ዓመቱ በጠቅላላው ብር 862,854.00 ወጪ ሆኗል፣

- 10 የመስከ ተሸከርካሪዎች የመድን ሽፋን ስለነበራቸው ተጠግነው ወደ ሥራ የተሰማሩ ሲሆን፣ ሌሎች 19 ተሸከርካሪዎች ( 10 በመንግሥት በጀትና 9 በመድን ሽፋን) በጥገና ላይ ይገኛሉ፣

- የባለሥልጣን መ/ቤቱ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለተሸከርካሪዎች በጠቅላላው ብር 65,215.95 ለነዳጅና ቅባት ወጪ ተደርጓል።

## 8.3 የሕትመት ዋና ክፍል

የመ/ቤቱ የሕትመት ዋና ክፍል ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ መስከረም 30 ቀን 1994 ዓ.ም ጊዜ ውስጥ 25,751 የተለያዩ ዓይነት ጥራዞች፣ 6,711,287 ገጽ ያላቸው ሕትመቶች አትሞ ለሚመለከተው ክፍል ያቀረበ ሲሆን፣ ከተለያዩ ክፍሎች ለሚቀርቡለት የፎቶኮፒ አገልግሎት ሰጥቷል፣

## 8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

### ሀ. በማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

- ለኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተዘጋጁ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች ማለትም በራሪ ጽሑፎች፣ ፖስተሮች፣ መፈክሮች፣ መዝሙርና የቪዲዮ ክር ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለመገናኛ ብዙሃን ( ለኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት) እንዲደርስ በማድረግ ለቅስቀሳ ተግባር እንዲውሉ ተደርጓል፣

- ለግብርና ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ከተመረጡት ድራማዎች "ናሙና" የተሰኘው ድራማ ለቴሌቪዥንና ለሬዲዮ ስርጭት በሚያመች መልኩ

እንዲዘጋጅ ለማድረግ በጨረታ ካሸነፈው ወገን ጋር ውል ለመፈፀም ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ተደርጓል፡፡

- ስለ ግብርና ቆጠራው ዓላማ፣ ይዘት፣ አጀማመር... ወዘተ በተመለከተ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊዎች መግለጫዎችን በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ተችሏል፡፡

- በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጁ 1,450 ሪፖርቶች ለ270 መ/ቤቶችና መረጃ ተጠቃሚዎች በነፃ እንዲሰራጩ የተደረገ ሲሆን፣ 798 ሪፖርቶች ደግሞ በብር 23,106.10 ሺያጭ ተፈጽሟል፡፡ በሩብ ዓመቱ በጠቅላላው 2,248 ሪፖርቶች ስርጭት ተካሂዷል፡፡

- በሩብ ዓመቱ የመ/ቤቱ የስልክ ማውጫና የ1994 የቀን መቁጠሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን፣ የመ/ቤቱ ብሮሸር ተዘጋጅቶ ለሕትመት ተዘጋጅቷል፡፡

- የመ/ቤቱ ቤተ መፃሕፍት ከውጭና ከመ/ቤቱ ለመጡ 900 ተጠቃሚዎች አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ከውጭና ከአገር ውስጥ ለመጡና መረጃ ለሚፈልጉ እንግዶች አስፈላጊው መረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡

<u>የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት</u>

- ለግብርና ቆጠራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ለማሟላት ከ13,000 በላይ በተለያዩ የሥራ መስክ ላይ የሚሳተፉ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር አስፈላጊው ፎርማሊቲ በማዘጋጀት ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተልኮ፣ ኮሚሽኑም የቀረበለትን ዶክመንት ከመረመረ በኋላ የተጠየቀው የሰው ኃይል ቅጥር እንዲፈፀም በመፍቀዱ የአብዛኛው ቅጥር ተፈጽሟል፡፡

- የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን በየጊዜው እያደገ በመምጣቱ ምክንያት ተጨማሪ የሰው ኃይል በቋሚነት እንዲቀጠር ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የቀረበው የ191 የሥራ መደብ ጥያቄ ምላሽ አግኝቷል፡፡ በመሆኑም ለተፈቀደው የሥራ መደብ የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ በመላኩ ውጤቱን በመጠባበቅ ላይ የምንገኝ ሲሆን፣ በተጨማሪ በሕግ አገልግሎት በኩል

የሚታየውን የሥራ መደራረብ ለመቅረፍ ተጨማሪ ሦስት የነገረፈጅ የሥራ መደብ ጥያቄ ቀርቧል፡፡

ሐ. <u>የሕግ አገልግሎት</u>

- የመ/ቤቱ ባልደረቦች በተለያዩ የኃላፊነት ቦታ ላይ በነበሩበት ጊዜ የተሰጣቸውን የመንግሥት ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በጠቅላላው ብር 49,676.76 ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ በሚመለከተው ፍርድ ቤት በኩል ስለተወሰነ ስለ አፈፃፀሙ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

- በተመሣሣይ ከሌሎች የመ/ቤቱ ሠራተኞች መ/ቤቱ የሚፈልግባቸውን በጠቅላላው ብር 50,473.92 ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት መ/ቤቱ ክስ መስርቶ ጉዳዩን በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡

- ሌሎች ሠራተኞች ከመ/ቤቱ እንዲከፈላቸው የጠየቁት የጉዳት ካሳ በጠቅላላው ብር 242,160 በሚመለከተው ፍርድ ቤት በኩል እየታየ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የብር 150,000 የጉዳት ካሳ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ጥያቄ ቀርቦ፣ ከሳሽ መልስ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

መ. <u>የኦዲት አገልግሎት</u>

- አገልግሎቱ የዋናው መ/ቤትንና የ22 ቱን ቅ/ጽ/ቤቶች የሚንቀሳቀሰውን በርካታ የገንዘብ ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ሂሳቡን በቅድሚያ እየመረመረ አስፈላጊውን ማጣራት እያከናወነ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ያደርጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለዋናው መ/ቤትና ለ22ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 37,722,875.80 ቅደመ ምርመራ አድርጓል፣ እንደዚሁም 13,264,332.28 ወጪዎችን ዝርዝር ምርመራ አካሂዶ፣ ሂሳቡ እንዲወራረድ አድርጓል፡፡

- በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ ገንዘብ በባንክ በኩል ሲላክ እና የተለያዩ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች የገንዘብ ጥያቄ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት በአገልግሎቱ ቅድመ ምርመራ አድርጓል፡፡

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ የመስክ ተሽከርካሪዎችን የነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ የነዳጅ ደረሰኝ ወጪ፣ በመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መሞላቱንና ተሽከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎሜትር እንደተጓዙ ቁጥጥር አድርጓል፣

- በተጨማሪ የሁለት ቅ/ጽ/ቤቶችን ማለትም የሚዛን ተፈሪ ገንዘብ ያዥንና የአዋሣ ጽ/ቤት የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞችን ርክክብ አስፈጽሟል።

ሠ. <u>የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት</u>

- መ/ቤቱ በ1994 በጀት ዓመት ሊያካሂዳቸው በዕቅድ የተያዙ የሁለት ፕሮጀክቶች (የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይና የግብርና ናሙና ቆጠራ) በጀት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎት ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል አስተላልፏል፣

- የመ/ቤቱን ወርሃዊ የፕሮጀክቶች የፊዚካልና ፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል አስተላልፏል፤

- ለ1995-97 የመ/ቤቱን የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ከባለሥልጣኑ የስታቲስቲክስ ጥናት ቅደም ተከተል በመነሳት የበጀት ፍላጎቱን ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ተደርጓል፣

9. <u>በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተሰጡ መፍትሄዎች</u>

ሀ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት በበጀት ዓመቱ በመላው ሀገሪቱ የጀመረው የግብርና ናሙና ቆጠራ ተግባር ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል በመጠየቁ በተለይም ለመስክ ሠራተኞች ትኩረት በመስጠት ከአጎራባች ክልሎችና ዞኖች ለመቅጠር ተሞክሯል። ሆኖም መ/ቤቱ የቆጠራ ሥራውን ለማቃናት ቀድሞ ከነበሩት 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በተጨማሪ 25 ጽ/ቤቶች ከፍቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፤ ለእነዚህና ለቀድሞዎቹ ጽ/ቤቶች የድጋፍ ሰጪ (የአስተዳደርና የፋይናንስ ሥራ) ሠራተኞችን ለመቅጠር ተሞክሮ እስከ አሁን ለማሟላት አልተቻለም። በመሆኑም ጽ/ቤቶቹ ባልተሟላ የሰው ኃይል እየተንቀሳቀሱ ሲሆን፤ የቴክኒኩን ሥራ እንዲያስተባብሩ የተመደቡ ባለሙያዎች የአስተዳደሩን ሥራ ደርበው እንዲሰሩ በመደረጉ አስፈላጊ ያለሆነ የሥራ ጫና ተፈጥሯል፣

ለ. የባለሥልጣኑ የሥራ ስፋት በየዓመቱ እየጨመረ በመሄዱ በርካታ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ቀጥሮ በማሠራት ላይ ይገኛል። በየጊዜው በሚቀርበው የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሪፖርቶችና የበጀት ፍላጎት ጥያቄ ላይ አሁን ካሉት ቢሮዎች በተጨማሪ በዛ ያሉ ክፍሎች የሚኖሩት ቢሮ እንዲያገኝ ወይም በግንባታ እንዲያሟላ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ባለመሆኑ በከፍተኛ የሃገር ሀብት የተማሩ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ተስማሚ የሆነ የሥራ ቦታ ባለማግኘታቸው ሥራውን በተፈለገው ሁኔታ ማከናወን አልቻሉም። እንደዚሁም በተለያዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በቂ ቢሮዎችና መጋዘኖች ቢያስፈልጋቸውም ማሟላት አልተቻለም፣ ስለሆነም ይህ የቢሮና የቦታ ጥበት ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል፡፡

ሐ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚያካሂዳቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ጥናቶች ከፍተኛ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚጠይቁ በመሆናቸው መ/ቤቱ በየጊዜው ያሉትን ባለሙያዎች ለከፍተኛ ትምህርትና የተለያዩ ዓለማቀፋዊ ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶችና የምርምር ሪፖርቶች በሚቀርቡበት ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ በማድረግ ያላቸው ልምድ የሚያካፍሉበትንና ተጨማሪ ተሞክሮዎች የሚያገኙበትን ሁኔታ እያመቻቸላቸው ይገኛል። ሆኖም ለእነዚህ ባለሙያዎች አሁን የሚከፈላቸው ደመወዝ በተመሳሳይ ደረጃና ሙያ ካላቸው ሌሎች ድርጅቶች ከሚሠሩ ባለሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ለተሻለ ክፍያ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎቹ መ/ቤቱን እየለቀቁ ይገኛሉ። ስለዚህ መንግስት ይህንን ችግር ለዘለቄታው መፍታት እንዲቻል ለመ/ቤቱ ልዩ የደመወዝ ስኬል እንዲፈቀድ እንጠይቃለን፡፡

መ. በባለሥልጣኑ መ/ቤት አሁን ባለው አወቃቀር በተወሰኑ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ላይ አስፈላጊ ያልሆነ የሥራ ጫና የተፈጠረ በመሆኑ በተለይም 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በአንድ መምሪያ ከዋናው መ/ቤት ለመቆጣጠርና ለመምራት አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ ሌሎች ቴክኒካል መምሪያዎችንና አገልግሎቶችን ከ22ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር መምራት የሚችል በም/ዋና ሥራ አስኪያጅ ደረጃ መ/ቤቱ በተጨማሪ ቢዋቀር የተሻለ እንደሚሆን ተገንዝበናል። ስለዚህ የመ/ቤቱን መዋቅር በአዲስ መልክ ለመለወጥ እንዲቻል በባለሙያዎች የሚጠናበት ሁኔታ በመንግሥት እንዲመቻች ወይም ከዚህ በፊት መ/ቤቱ የነበረው መዋቅር መሻሻል ተደርጎበት እንደገና በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡